"እዎ ፡ ጌታዬ ፡ ምስጋና ፡ ይግባዎል !" አሉ ፡ ወይዘሮ ፡ ጥሩ ።

" እዎ ፡ እልማችን ፡ ምኞታችን ፡ ሞላ ፡ ደስ ፡ ይበለን ፡ ጥሩዬ ! "

" የኛስ ፡ እልማችን ፡ ሞላ ፡ ነገር ፡ ግን ---"

" ነገር ፡ ግን ፡ ምን ?"

" እንዲያው ፡ የሰዎን ፡ ሁኔታ ፡ ስመለከት ፡ በደስታዬ ፡ መሀከል ፡ ፍራትና ፡ እዘን ፡ ይሰነቀራል ።"

" ድሮውንስ ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ከናት ፡ ካባትዋ ፡ ስትለይ ፡ ደስ ፡ ብሎዋት ፡ ተለይታ ፡ ታውቃለች ? አንቺ ፡ ወደኔ ፡ ስትመጪ ፡ እያለቀስሽ ፡ መምጣትሽን ፡ ረሳሽው !"

" የሰም ፡ የሰዋ ፡ ልዩ ፡ ነው ፡ ጌታዬ ።"

"ምንም ፡ ልዩ ፡ አይደለም ፡ ቆይ ፡ አሁን ፡ መልስ ፡ ጠርተናት ፡ ስትመጣ ፡ ጭራሽ ፡ ተለውጣ ፡ ደስ ፡ ብሎዋት ፡ ያላገኘሻት ፡ እንደ ሆነ ፡ ምን ፡ አለ ፡ ትይኛለሽ !"

" እስቲ ፡ እንዳፍዎ ፡ ያርግልን !"

" ይህን ፡ አትጠርጥሪ ፡ ግዴለሽም ። "

" አሁን ፡ ደግሞ ፡ ብሶባታል ፡ ከማልቀስ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ስራ ፡ የላትም ።"

"መልያያው ፡ ቀን ፡ ስለ ፡ ደረሰ ፡ ነዋ ! ሌላ ፡ ምን ፡ መሰለሽ!

" እሱም ፡ ይሆናል ፡ ደግሞ ፡ ከሱ ፡ ሌላ ፡ በቀደም ፡ አባ ፡ ተክለ ፡ ሀይማኖት ፡ ቤተ ፡ክርስቲያን ፡ በሄዱበት ፡ ካሳ ፡ ዳምጤ ፡ መጥቶ ፡ አብሮዋት ፡ ቆይቶ ፡ ከሄደ ፡ ወዲህ ፡ ጭራሽ ፡ ባሰባት ፡ አሉኝ ።"

" ካሳ ፡ ዳምጤ ፡ በጭራሽ ፡ እዚህ ፡ ቤት ፡ እንዳይደርስ ፡ አላልሁም ፡ ኖሮዋል ? ለምን ፡ መጣ ?"

"ያነለት ፡ ያሰኘውን ፡ ሰይጣን ፡ እንጃለት ፡ እንጂ ፡ ቤታችን ፡ እርም ፡ ብሎ ፡ ከተወው ፡ስንት ፡ጊዜው ፡ ነው ? ጌታዬ !"

" መነኩሴውም ፡ አይረቡም ፡ እባክሽ ! ሰው ፡ ያለቅጥ ፡ መጠጥ ፡ ከወደደ ፡ አይረባም ። በመጠጥ ፡ አባብሎ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሄድሁ ፡ እንዲሉ ፡ አድርጎዋቸው ፡ ይሆናል ።"

" እሱስ ፡ አይመስለኝም ፡ ከካሳየ ፡ ጋር ፡ ተስማምተው ፡ ያደረጉት ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ያዩትን ፡ ሁሉ ፡ እንዲያ ፡ አዝነው



አይነግሩኝም ፡ ነበር ።"

" ምን ፡ አዩሁ ፡ አሉ ?"

" ካሳየን ፡ በስርቆሽ ፡ በር ፡ ሲወጣ ፡ አዩሁና ፡ እቤት ፡ ብገባ ፡ ሰብለን ፡ ወረቀት ፡ እያነበበች ፡ ስታለቅስ ፡ አገኘሁዋት ፡ አሉ ።"

"የምን ፡ ወረቀት?" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ ደንግጠው ።

"ምን ፡ አውቃለሁ? አባ ፡ ተክሌ ፡ ከነገሩኝ ፡ በሁዋላ ፡ ብጠይቃት ፡ የተማርሁትን ፡ እንዳልረሳ ፡ ጽፌ ፡ የማጠናበት ፡ ነው ፡ አለችኝ ።"

"እሳይኝ ፡ አላልሻትም?"

"ብዬት ፡ ነበር ፡ ጣልሁት ፡ አለችኝ ።"

"በይ ፡ ተይው ፡ ግዴለም ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ማለፊያው ፡ ደርሶዋል ።" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ ትንሽ ፡ ሲያስቡ ፡ ቆይተው ፡ ሲነሱ ።

በጎጃም ፡ የላገባች ፡ ልጃገረድ ፡ ቆንጆ ፡ ያገባች ፡ ሴት ፡ በገኝ ፡ ትባላለች ። የቆንጆና ፡ የበገኝ ፡ መለያ ፡ ከሆኑት ፡ ምልክቶች ፡ አንዱ ፡ መታጠቂያቸው ፡ ነው ። የበገኞች ፡ መታጠቂያ ፡ መቀነት ፡ ሲሆን ፡ የቆንጆዎች ፡ መታጠቂያ ፡ ሚር ፡ የሚባል ፡ ጠፍር ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ የሰርጉ ፡ ዋዜማ ፡ ማታ ፡ ሙሽራዋ ፡ ከቆንጆነት ፡ኑሮ ፡ ወደ ፡ በገኝነት ፡ ኑሮ ፡ ለመተላለፍ ፡ የምትጀምርበት ፡ በመሆኑ ፡ ሆማም ፡ የሚር ፡ መፍቻም ፡ ይባላል ።

በዚያነለት ፡ የተጠራው ፡ ሁሉ ፡ መኳዋንንት ፡ ወይዛዝር ፡ ሽማግሌው ፡ ባልቴቱ ፡ ቆንጆው ፡ ጎረምሳው ፡ ልጁ ፡ የሚር ፡ መፍቻ ፡ የሚባለውን ፡ ሰፋ ፡ ያለ ፡ ቦታ ፡ ከቦ ፡ የሚቀመጠው ፡ ተቀምጦ ፡ የሚቆመው ፡ ቆሞ ፡ ሲጠብቅ ፡ ሙሽራዋ ፡ ሚርዋን ፡ እንደማይፈታ ፡ አድርጋ ፡ ውሉን ፡ አሳጥታ ፡ ተብትባ ፡ በቆንጃጅቱ ፡ ታጅባ ፡ ትመጣና ፡ ተመልካቹ ፡ በከበበው ፡ ቦታ ፡ ገብታ ፡ ትቀመጣለች ። ከዚያ ፡ ከቆንጃጅቱ ፡ መሀከል ፡ የሙሽራዋን ፡ የተተበተበ ፡ ሚር ፡ ለመፍታት ፡ ብርቱዋ ፡ ትመረጥና ፡ እሰዋ ፡ ለመፍታት ፡ ሙሽራዋ ፡ ላለማስፈታት ፡ ትግል ፡ ይጀመራል ። ሙሽራዋና ፡ ሚር ፡ ፈችዋ ፡ ደክመው ፡ እስኪያልባቸው ፡ ሲታገሉ ፡ የከበባቸው ፡ ሰውም ፡ ትግላቸውን ፡ እዩተመለከተ ፡ ሲስቅና ፡ ሲያወካ ፡ ብዙ ፡ ቆይቶ ፡ በመጨረሻ ፡ ሚሩ ፡ ሲፈታ ፡ እዚያ፡

